# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

ሚያዚያ 23 ቀን 2005 ዓ. ም. 1 May 2013

## ወገንተኝነትን የሚጠይቅ ቀንን
## ስንዘክርና ስናከብር

አለም አቀፍ የሰራተኞች ቀን በሰራተኞች፡ በላብ አደሮችና በሰላም ወዳድ ኃይሎች ሁሉ በየአመቱ እየተከበረ የሚገኘው እነዚህ ኃይሎች በነፃ የመደራጀትና ለጥቅማቸው ለመታገል ያላቸው መብት እንዲከበር ብቻ ሳይሆን በትግል የተጎናፀፏቸው ድሎች እንዳይቀለበሱ ነቅቶ ለመጠበቅ፡ ያልተሳኩት ደግሞ እንዲከበር በፅናት ለመታገል ቃል በመግባት ሲሆን ለነዚህ መብቶች መከበር ሲሉ የተሰዉትን እየዘከረ፡ የግፍ ፅዋ የተጎነጩትን፡ ለስደት የተዳረጉትንና ደብዛቸው የጠፋውን ሁሉ ተገቢ ክብራቸውን እየለገሰ ትግላቸው፡ ተግባራቸው፡ ሕያው መሆኑን በደስታም በሀዘንም እያስታወሱ ለመጪው ትውልድ በመልካም እሴትነት ለማስተላለፍ ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ ለመብታቸው መከበር በታገሉ ለእስር የተዳረጉ ጽናቱን እንዲሰጣቸውና በነፃ ተለቀው በሰላም ከወዳጆቻቸውን ከትግል ጓደኞቻቸው ጋር እንዲቀላቀሉ ያላቸውን ቁርጠኛ ትግል ለመቀጠል ቃል ኪዳናቸውን በማደስ ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ ላብ አደርና ሰራተኞች ለመብታቸው መከበር ሲሉ በርካታ አባላቱንና እንደነ አበራ ገሙ፡ ማርቆስ ኃጎስን የመሰሉ መሪዎችና ሌሎችም ጠንካራ ታጋዮቹ ከፍተኛ መስዋዕት የከፈሉ ቢሆንም ይህንን ቀን ደማቸውን ባፈሰሱበትና አጥንታቸውን በከሰከሱበት በሀገራቸው መብታቸው ስላልተረጋገጠላቸው በሰላም ለማክበር ላለፉት በርካታ አመታት የሚቻላቸው ሆኖ አልተገኘም። ፍላጎታቸውን፡ ጭንቀታቸውን፡ ስሜታቸውን፡ ችግራቸውን፡ በደላቸውን፡ ለሕዝባቸው ከፍ ሲልም በአለም አቀፍ ደረጃ ለሚገኙ ሰላም ወዳድ ኃይሎች በግልፅ ሊያሰሙና ድጋፋቸውን ሊጠይቁ አይቻላቸውም።

በዛሬው እለት ይህንን ቀን ስናከብርና ስንዘክር በተለይ በሚያዚያ 21 ቀን በወታደራዊው አምባገነን አገዛዝ ከ 1500 በላይ የሆኑ ተማሪዎች፡ አስተማሪዎች፡ ሰራተኞችና ላብ አደሮች በተለይም ደግሞ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በግፍና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ የተጨፈጨፉትን በማስታወስ ጭምር ነው። ታሪክ በታሪክነት ተፅፎ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፍ ከተባለ የኢትዮጵያ ላባደሮችና ሰራተኞች የደረሰባቸውና እየደረሰባቸው ያለው ጭቆና፡ በደልና ብዝበዛ በወያኔ ዘረኛው አገዛዝ ከምንጊዜውም በላይ የከፋ እንደሆነ የእድሜ ባለፀጋ ሆነው ሶስቱንም አገዛዞች የታገሏቸው ቀርቶ የኢትዮጵያን ሁናቴ በቅርበት የሚከታተሉ ባዕዳኖች እንኳ የተገነዘቡት ለመሆናቸው ከሚያወጡት ፁሁፎቻቸውና ድረገፆቻቸው

EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
92270 Bois Colombes
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645

ለመረዳት አያዳግትም። የላብ አደርና ሰራተኞች የድርጅት መሪዎቻቸውንና ጠንካራ አባሎቻቸውን በስውርና በግልፅ በማሰርና በማንገላታት፡ ለስደትም እንዲዳረጉ በማድረግ ከዛም ድርጅታቸውን ማፍረስና በተለጣፊ መተካት፡ ቀጣሪዎቻቸው በነሱ ላይ እንዳሻ እንዲፈነጩባቸው በመፍቀድ መብት አልባ ኑሮ እንዲኖር መዳረግ አሁንም ድረስ እየቀጠለ ያለ ሁኔታ ነው።

„ሰነፍና ልግምተኛ“ ተብለው እንዲሰደቡ የሀገሩን ዜጋ ያውም አስተዳድረዋለሁ፡ የኑሮ ሁኔታህን አሻሽልልሃለሁ ለሚለው ሕዝብ ለተለያዩ ዘረኝነትን ያዘለ፡ ኢሰብአዊነት የተጠናወተው እንዳሻ የመደብደብ እርምጃና የውርደት ድርጊት በቻይና ቀጣሪዎቻቸው እንዲደርስባቸው የፈቀደ አገዛዝ በታሪካችን የወያኔ አገዛዝ ብቸኛውና የመጀመሪያውም ነው። ማንኛውም ሰራተኛ በተለያዩ የሀገሩ አካባቢዎች ሰርቶ ለመኖር ያለውን የዜጋዊ መብቱን የነፈገ እንዲሁ ወያኔ ነው። የኤኮኖሚ እድገት አስገኝቼልሃለሁ ከሚለው ላብ አደርና ሰራተኛ ይልቅ የበለጠ ጥብቅና እየቆመ ያለው ለባዕዳን ደጋፊዎቹ ለመሆኑ የሚወስዳቸው እርምጃዎቹ በሙሉ የሚመሰክሩበት ነው። መብታቸው ተረግጧልና ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍና በአል ነክ የሆኑ የተለያዩ ትርኢቶችንና ፁሁፎችን በማዘጋጀት በአደባባይ በግልፅ ሊያከብሩት የወያኔ አገዛዝ በገነባው የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ አልተቻላቸውም። በተለያዩ ጊዜያት የደረሰባቸው የአፈናና የበደል እርምጃ በአስፈሪ ሰቀቀን ውስጥ ተሸማቀው እንዲኖሩ ዳርጓቸዋል። እርስ በርስ እንዳይተማመኑ ሆን ብሎ ለመከፋፈል ያመቸው ዘንዳም የጥላቻ ፖለቲካ በመሃላቸው መንዛት ብቻ ሳይሆን አንድነታቸውን መልሰው እንዳይገነቡ የጎሳ መርዝ ነስንሶባቸዋል።

ሁሉን ተጠቃሚ ያደረገ የኤኮኖሚ እድገት ተገኝቷል ተብሎ በሚለፈፍበት፡ በየጊዜው ወደላይ እያሻቀበ በሚሄደው የዋጋ ንረት፡ ማቆሚያ ባጣ ሙስና፡ በኑሮ ውድነት፡ በመልካም አስተዳደርና በመብት እጦት ምክንያት ከምንጊዜውም በላይ የሚራበው፡ የሚጠማው፡ የሚለብሰውን የሚያጣውና በዚህም ክፉኛ እየተጎሳቆለ የሚገኘው የላብ አደሩና የሰራተኛው ቁጥር በርካታ ነው። ሴት ሰራተኞችና ላብ አደሮች ለእኩል ሥራ እኩል ደሞዝ የማይከፈላቸው ብቻ ሳይሆን ይብስኑ በአገዛዙ ዋና አቀናባሪነት ለዘመናዊ ባርነት ወደ አረብ አገር እንዲጓዙ እያደረገ ያለና የሀገሩን ዜጋ በመሸጥ እየከበረ ያለ መሰሪ ቡድን ነው።

ሁሉን አሳታፊና ተጠቃሚ እያደረገ ያለ የኤኮኖሚ እድገት እየተባለ የአገዛዙን እድሜ ለማስረዘም ሲባል መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ እየተነዛ ቢገኝም በላባደሩና ሰራተኛ የኑሮ ሕይወት ላይ ግን መሰረታዊ ለውጥ የሚታይ ሊሆን አልቻለም። ላብ አደሩና ሰራተኛው የሚፈልገው ተገኘ የሚባለው የኤኮኖሚ እድገት አሃዙ በየጋዜጣው ተቀምጦ እንዲያየው ወይንም ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን እስኪሰለቸው

EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
92270 Bois Colombes
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

ድረስ እየተለፈለፈበት በጆሮው እንዲያዳምጠው ሳይሆን በተጨባጭ ያለበትን የኑሮ ሁናቴ ተረድቶለት የሚቀይርለት ወይንም ደግሞ ራሱ በራሱ ጥረት ለመቀየር የሚያስችለው ምህዳር እንዲመቻችለት ነፃነቱን አለመነፈግ ነው። የንግድ ጤናማንትና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል አሰፈንን ተብሎ በሚነገርበት ሀገር ላብ አደሩና ሰራተኛው እየተራበ፡ እየተጠማና እየታረዘ የሚቀመስ አጥቶ ገነባን ከሚሏቸው ሕንፃ አጥር ሥር ለጎዳና ሕይወት ለመኖር መዳረጋቸውንና ጥቂቶች ይበልጥ በህብት ክምችት የሚሽሞነሞኑበት ሁናቴ ነው እያየ የሚገኘው።

ታዲያ በዛሬው እለት ይህንን የዘንድሮውን አለም አቀፍ የሰራተኞች ቀን የምናከብረውና የምንዘክረው በላብ አደሩና በሰራተኛው ላይ እየደረሰ ያለውን ብዝበዛና ጭቆና እንዲሁም ከመብት አልባ ኑሯቸው የሚገላገሉበትን ፍቱን መፍትሄ በማሰላሰል ሲሆን የላብ አደሩና የሰራተኛው ክፍል የዴሞክራሲ መብታቸውንና ነፃነታቸውን ለመጎናፀፍ የሚያደርጉትን ትግል በቁርጠኝነት በመደገፍና ከጎናቸውም አብረን የምንታገል ለመሆናችን የገባነውን ቃል ኪዳን ዛሬም በማደስ ነው። ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎችም ይህንን ትግላቸውን በመደገፍና ለስኬት እንዲደርሱም የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ኢሕአፓ የትግል ጥሪውን ያቀርባል።

የሰራተኛውን የላብ አደሩ ትግል ይለምልም!!
በፀና ትግላችን እናቸንፋለን!!


EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
92270 Bois Colombes
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645